# “ፈረንጅ አምላኩ…” ማን ነው? ፩ኛ

ገ/ኢ. ጐርፉ

ዛሬ በሃገራችን አንድ ሰው በራዲዮም ሆነ በቴሌቪዥን ሓሳቡን ለመግለጽ ሲቀርብ ለሰፊው ሕዝብ እንደሚነጋገር እንዳለ የተዘነጋ ይመስላል። ሰፊው ሕዝብ ከራሱ ቋንቋ ይልቅ የእንግሊዝኛን ቃላት ጣል-ጣል አድርገው እየቀየጡና እየቀላቀሉ ሲናገሩት በይበልጥ እንደሚገባው አድርገው ያወቁ ሰዎች የሚናገሩ ያሉ ነው የሚመስል። ይህም በግል ድርጅት ሰዎች ሆነ በመንግሥት ባለስልጣኖች እንደፋሊጥ ተቆጥሮ የሚዘወተር ነገር ሆኗል።

እርግጥ፣ አሁን እንደ ጠቀስናቸው፣ ማለትም፤ እንደ ራድዮና ቴሌቪዥን የመሳሰሉትን ቃላት በሰፊው የተለመዱና በቋንቋችን ተኪ ቃል የሌላቸው ከሆነ፣ ገና አዲስ ቃል ፈጥሮ እንዲለመድ ከመልፋት ይልቅ የተለመዱትን ቃላት መጠቀም ደግ ነው። ግን አንድ ቀላል ሓሳብ ለመግለጽ የራሳችን ቃላት በቋንቋችን እያሉን የፈረንጁን ቃላት ቀላቅሎ መጠቀሙ ምሁር፣ ወይም ዐዋቂ መስሎ ለመታየት ነው፣ ወይስ ለምን ይሆን?

በየከተማውና በየባላገሩ የተያዘው ዘዴ ደግሞ ከሻሂ ቤትና ከቡና ቤት ጀምሮ እስከ ሆቴሎችና የቴክኒክ ትምህርት ቤቶችም ጭምር በውጭ ሃገር ስም መጥራት እንደ ትልቅ ፋሊጥ ሆኖ ተይዟል። የሃገር ወንዞች፣ ተራሮች፣ የታላላቅ ጀግኖች፣ የጥንታውያን ገዳማትና የቅዱሳን ቦታዎች ስም በብዛት አሉን። ስም ሳይጠፋ የውጭ ሃገር ስም ማውጣቱ ከቶ ለምንድነው?

የውጭ ፋሊጥና ዘዴ ሁሉ መልካም እንዳልሆነ ማወቅ ይገባናል። ደጉንና መጥፎውን አመዛዝኖ ደግ-ደጉን መያዝ፣ የማይረባውንና የማያስፈልገውን መጣልና ማስወገድ፣ በራሳች ቃላትና ቋንቋም ለመጠቀም መታገል እጅግ አስፈላጊ ነው። ሁሉም በየቦታው ሲሆን ያምራል፣ ይህም ማለት አማርኛ ስንናገር በጠራ አማርኛ መናገር፣ እንግሊዝኛ ስንናገርም በጠራ እንግሊዝኛ መናገር ይገባናል እንጂ አንዱ ከሌላው መቀየጥና መቀላቀሉ ለምንድነው? የውጭ ቋንቋን ለማያውቅ ሰው ከማደናገር አልፎ የፈረንጅ አምልኮን የማስፋፋት ዓላማ እንጂ ሌላ ምንም ጥቅም የለውም። ቋንቋው በእንደበታችን ነው፣ የጠራ ንግግር ከመናገር ማን ይከለክለናል?

በልጅነቴ አባቴ፡ “ኢትዮጵያ የፈረንጁን ጎረምሳ እስከነንፍጡ ዐቅፋ ሳመችው!” ሲሉ ስሰማ ምን ማለታቸው መሆኑ ዛሬ ነው እያደር የሚገባኝ ያለው። ዛሬማ የባሰበት ይመስላል። የራሳችን የሆነውን ንቀን የፈረንጁን ግን አክብረን መያዝ ራሳችንን ማዋረድና ስሕተት ነውና ይህ በቶሎ መታረም ይገባዋል። ራሴን በራሴ፣ አፌን በምላሴ ተብሷል።

**ይቀጥላል…**

# “ፈረንጅ አምላኩ…” ማን ነው? ፪ኛ

ገ/ኢ. ጐርፉ

ከታወቀ የአዲስ አበባ ሆስፒታል ሲሠራ የነበረ አንድ ሓኪም ያጫወተኝን አልረሳውም። አብረውት የሚሠሩ ፈረንጅ አስታማሚዎች ነበሩት። ታድያ በተደጋጋሚ የደረሰብኝ ሁኔታ ነው እያለ፣ ሕመምተኞቹ፤ “ለምን ነጩ አያክመኝም?” “አንተ አትንካኝ!” “እሱ ይመርምረኝ” ሲሉኝ፣ ”እሱማ አስታማሚ ነው፣ ዶክተሩ እኮ እኔ ነኝ” ብላቸው፣ “ግድ የለም፣ እሱ ነጭ ነው፣ እሱ ቢያክመኝ ይሻለኛል…” የሚሉ በዙዎች ነበሩ፣ ብሎ ነገረኝ።

ሌላም የቅርብ ቤተ-ዘመድ የሆኑ አዛውንት ወደ አሜሪካ መጥተው በመኪና ስንሽራሽር ከመንገድ አንድ ነጭ ለማኝ አዩና፤ “ነጩ! አሜሪካዊው! እንዴት ይለምናል!” በማለት ፈጽሞ ማመን አቃታቸው። “አባባ፣ ቆዳው ነጭ መሆኑ ምን ፋይዳ አለው? ማንም ሰው የሚረባ ትምህርት ሆነ ችሎታ ከሌለው ሠርቶ ሊበላ አይችልም። ያለው አማራጭ ታድያ ከመንገድ ቆሞ ልመና ብቻ ነው።” አልኳቸው። ቀኑን ሙሉና ሰሙኑንም በዚህ ሁኔታ ሲገረሙና ሲደነቁ ሰነበቱ። አገር ተመልሰውም ወሬያቸው ሁሉ ስለዚሁ ለማኝ ጉዳይ እንደ ነበር ሰማሁ።

ይህንና ይህን የመሳሰለ ነገር በሃገራችን ሰዎች ተደጋግሞ ሲፈጸምና ሲነገር ስናይ፣ “ሓበሻ ኩሩ ሕዝብ ነው፣ በኮሎንያሊዝም ስላልተጠቃ ለነጭ ሰው አያጎበድድም…” እያሉ አጉል ጉራ መንዛት ምን ፍሬ አለው? ሕመማችንን ማመንና መድሓኒትም በቶሎ መፈለጉ አይሻለንም ወይ?

በሃገራችን የባኅል ሚኒስተር መሥሪያ ቤትና ጽሕፈት ቤት አለ፣ ከዚህ ላይ ታድያ ሓላፊነቱና ተሳትፎው ምንድነው? የውጭ አገር ቋንቋና ትምህርት መማር እጅግ ጠቃሚ ነው፣ ግን ሌሎች የሰለጠኑ ሃገሮችን ብናይ የገዛ ራሳቸውን ባኅል እየተዉና እያንቋሸሹ እኮ አይደለም የሰለጠኑት። ከቻይናና ከጃፓን ማየትና መማር ይበጃል። የራሳችን የሆነውን ባኅል ብንመለከት ደግሞ ባኅላችን ሙሉ በሙሉ መልካም ነው ማለት አይደለም። በባኅላችንም የሚገኙ ተግባሮችን ሁሉ መመርመርና ደግ-ደጉን አጥብቀን መያዝ፣ የማይረቡትን ወይም የሚጎዱትን የባኅል ርዝራዦችን ደግሞ አርቀን ማስወገድ ይገባናል።

የዘመኑ ተማሪዎች ትምህርት በራሳቸው ቋንቋ መማር ስለሚጀምሩ የራሳቸውን ባኅል ለማጥናት ዛሬ አመቺ ጊዜና ሁኔታ ነው። ሰው በልጅነቱ ባኅሉን ይዞ ሲያድግ በራሱ ባኅል እንዲኮራ፣ ደጉንና ደግ ያልሆነውንም እንዲመረምር ዕድል አገኘ ማለት ነው። በራስ ባኅል መኩራት ከፈረንጅ አምልኮ ለመዳን ይረዳል። ቀጥሎም በቅን መንፈስ የራስን ባኅል አስተውሎ መመርመር፣ መርምሮም የማይረባውንና የሚጎዳውን ማስወገድ የሚገባ ነው።

**ይቀጥላል…**

## "ፈረንጅ አምላኩ…" ማን ነው? ፯ኛ

ገ/ኢ. ጐርፉ

ሌላው ዓብይ ችግር ሆኖ ሳይፈታ በይደር ተቀምጦ ያለው የሃገር እክል ከኤርትራ ጋር ባለው የጠረፍ ጉዳይ ነው። በዚያም ላይ ግልጽ የሆነ የፈረንጅ አምልኮ ሁኔታ ታይቷል። ጠረፉን ተወልደው ያደጉበት፣ ከየትኛው ኮረብታ ተነስቶ እስከ የትኛው ግራር፣ ከየትኛው ወንዝ ዳርቻና መሸጋገሪያ እስከ የትኛው ቆጥና ዲንጋይ መሆኑን ቆጥረው፣ አበጥረው፣ አንጠርጥረው የሚያውቁ የድንበሩ ተወላጆች መኖራቸው አይሳትም። ይህ እንደ ማንኛውም የሃገር ድንበር እንጂ ልዩ የሚያርገው ነገር የለውም።

እንግድያው የድንበሩ ተወላጆች፣ በዕድሜ የበሰሉ አሮጊቶችና ሽማግሎች ስለ ድንበሩ ተጠይቀዋል ወይ? መጠየቅም ሆነ ለጠበቆችና ለሕግ ሰዎች ቃላቸውን የሰጡበት፣ ያማከሩበትም ጊዜ የለም። ይህ ብቻም አይደለም፤ ኢትዮጵያ ወደ ዓለም ሸንጎ፣ በሄግ ፍርድ-ቤት ወክለዋት የቀረቡ ሰዎች እነማን ናቸው ብለን ስንጠይቅ የሚከተለውን የስም ዝርዝር እናገኛለን፦

**The Federal Democratic Republic of Ethiopia, represented by*:**
**Counsel and Consultants**

**1.** Mr. W. DeVier Pierson, Piper Rudnick LLP, Washington, D.C.; Member of the Bar of the District of Columbia; Member of the Bar of the Supreme Court of the USA.
**2.** Professor Sean D. Murphy, George Washington University Law School, Washington, D.C. Member of the State Bar of Maryland
**3.** Mr. Don C. Lewis, Piper Rudnick LLP, Washington, D.C.; Member of the Bar of the District of Columbia; Member of the State Bar of Texas
**4.** Mr. Edward B. Rowe, Piper Rudnick LLP, Washington, D.C.; Member of the Bar of the District of Columbia; Member of the State Bar of Colorado
**5.** Ms. Virginia C. Dailey, Piper Rudnick LLP, Washington, D.C.; Member of the Bar of the District of Columbia; Member of the Law Society of England & Wales; Member of the State Bar of Florida
**6.** Mr. Thomas R. Snider, Piper Rudnick LLP, Washington, D.C.; Member of the Bar of the District of Columbia; Member of the State Bar of Massachusetts
**7.** Mr. Won Kidane, Piper Rudnick LLP, Washington, D.C.; Member of the Bar of the District of Columbia; Member of the State Bar of Illinois
**8.** Ms. Christina Evans, Piper Rudnick LLP, Washington, D.C.; Consultant

ከነዚህም የበላይ ሓላፊ በመሆን የተሳተፉ በኔዘርላንድ የኢትዮጵያ ኤምባሲ ሦስት ኢትዮጵያውያን ሠራተኞች ሲኖሩ፣ ሌሎቹ ግን ከሚስተር ዎን ኪዳኔ በቀር ሰባቱም የውጭ ደሞዝተኞችና ለገንዘብ ጥቅም ብቻ የቆሙ ነበሩ። ይህም ማለት ኢትዮጵያ ረታችም፣ ተረታችም ክፍያቸው በምንም የማይቀርባቸው የውጭ ቅጥረኞችን ይዘን ነበር ከዓለም ሸንጎ የቆምነው ማለት ነው። ታድያ፣ ችሎታ ያላቸው ኢትዮጵያውያን ጠበቆች የሉም? መልሱ፤ የፈረንጅ አምልኮ ሆነ እንጂ፣ ሰው መች ጠፋ? ብዙዎች ነበሩ!

**ይቀጥላል…**

* Source:- http://www.pca-cpa.org/upload/files/Eritrea%20Central%20Front%20award.pdf

# "ፈረንጅ አምላኩ…" ማን ነው? ፫ኛ

ገ/ኢ. ጐርፉ

የሃገሩና የጠረፉ አካባቢ ኗሪ ሕዝብ ስለ ጉዳዩ ቢጠየቅ፣ በአማካሪነትም ተሳትፎ ቢሆን የተሻለ ውሳኔና ዕርቅም እንደሚገኝ አያጠራጥርም። ለዚህ ጉዳይ በአማካሪነት ሊጠሩ ይገባቸው የነበሩ ሁለት ሰዎችን እንጠቅሳለን።

የመጀመሪያው ሰው ነፍሳቸውን ይማረውና፣ ከሞቱ ገና ዓመት እንኳን ያልሞላ፤ ደጃዝማች ዶክቶር ዘውዴ ገብረ ሥላሴ ናቸው። በዕድሜያቸው ሙሉ በተለያዩ የመንግሥት ሥራዎች ያገለገሉ፣ በትምህርትና በሞያ ይህ ጐደላቸው የማይባሉ፣ በኢትዮጵያና በኤርትራ ስላለው የጠረፍ ጉዳይም ከማንም የበለጠ እንጂ ያላነሰ ዕውቀት የነበራቸው፣ የሕግ ጠበቆቹንም ለማማከር የበቁ ሰው ነበሩ። ለዚህ ጉዳይ ለማማከር እንኳን ሳይጠሩና ሳይጠየቁ ስለቀሩ ጉዳዩ ለትውልድ የሚተላለፍ ቋሚ ቁስል ሆኖ ቀርቷል!

ሌላው ደግሞ ገና በሕይወት ያሉ፣ ለጥቂት ዓሥርት ዓመታትም የትግራይ ገዢ የነበሩ ሲሆኑ፣ ራስ መንገሻ ስዩም ናቸው። እኝህ ሰው አሁን ካለው መንግሥት በፖለቲካ አስተያየት ቢለያዩም፣ ኢትዮጵያዊነታቸው ግን ከቶ ይማያጠያይቅ፣ በሃገር ድምበር ጉዳይ ደግሞ ሕይወታቸውን ለመሰዋት ቢሆንም ወደኋላ ዘወር ብለው ይወላውላሉ ተብሎ የማይጠረጠሩ ናቸው።

የትግራይ ገዢ በነበሩበት ጥቂት ዓሥርት ዓመታት ራስ መንገሻ ሥዩም ከዳር እስከ ዳር ድንበሩን ተመላልሰው ያዩትና የጎበኙት፣ የመንግሥት ግብርም ከየት እስከ ወዴት ድረስ ይሰበሰብ እንደነበር፣ የግዛቱን ጠረፍና ዳርቻ በደምብ አጥርተው የሚያውቁ ሰው ናቸው። እኝህን አዛውንት በሕግ አማካሪነት እንኳን መጥራትና ማቅረብ እንዴት ችላ ሊባል በቃ?

እነዚህን ሁለት አዛውንት ለምሳሌ ጠቀስን እንጂ ከድንበሩ ኗሪዎች ብዙ ሽማግሎችና አሮጊቶችን ማማከር ይገባ እንደነበር አያጠራጥርም። እሳት የላሱ ወጣት ኢትዮጵያውያን ጠበቆችስ ለምን በጉዳዩ ሳይሳተፉ ቀሩ? ስለ ታሪካችን ከመጻሕፍትና ከድሮ የጣልያን ካርታ ያጠኑ የፈረንጅ ጠበቆችን ብቻ ይዘን ከዓለም የፍርድ ሸንጎ በመቅረባችን የደረሰብን ጦስ ይኸው ዛሬ ለትውልድ የሚተላለፍ ነቀርሳ አትርፈናል። እጅግ አሳዛኝ ነገር ነው!

የፈረንጅ አምልኮ ከተራው ዘበኛ እስከ ከፍተኛ የመንግሥት ባለስልጣኖች በሃገር ገብቶ የሚያጠቃን ያለ ጽኑ በሽታ መሆኑን በተከታታይ ጽሑፎች አሳይተናል። በሽታችንን ለማከም መታገል ነው እንጂ ራሳችንን ከንቱ መደለል ምንም አይጠቅመንም። የፈርንጅ አምልኮ ከሃገራችን ይጥፋ!